859
አነ

ሰነድ

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION

ቀን ተሕሣስ 2 2 2012
Date
ቁጥር 4/04424/12
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት፣</u>

ጉዳዩ፡- <u>የዕቃ የመጋዘን ቆይታ ጊዜ ገደብ ስለሚራዘምበት ሁኔታ፤</u>

የጉምሩክ አዋጅ 859/2006 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1160/2012 አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዘው ወደ አገር ውስጥ የገባ ዕቃ ከማከማቻ መጋዘን ከገባበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት ቀን፣፤ በአየር ተጓጉዘው ለሚገቡ ዕቃዎች በአስር ቀን ውስጥ አስፈላጊው የጉምርክ ሥነ-ሥርዓት ተፈጽሞባቸው ከማከማቻው መውጣት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ በማሻሻያ አዋጁ አንቀጽ 13 የተደነገገ የጊዜ ገደብ በበቂ ምክንያት ኮሚሽኑ ሊያራዝም እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሰረት በየብስና በአየር ተጓጉዘው አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሰነዶች በጉምሩክ አቃጅ 859/2006 አንቀጽ 10 ንዑስ አንጽ 1 ላይ በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሰነዶች በተለያዩ ምክንያቶች ለዲክላራሲዮን አቅራቢው በማሻሻያ አዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማይቀርቡበት ጊዜ እና በሌሎች በቂ ምክንያቶች የጊዜ ገደቡን ማራዘም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም፡-

1. የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ገደብ ለማራዘም የሚያስችሉ በቂ ምክንያቶች፡-

   (ሀ) የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዋና ዋና ሰነዶች በባንክ በኩል ያልደረሱ ወይም ዘግይተው የደረሱ መሆኑ ከባንክ በሚቀርብ ማስረጃ ሲረጋገጥ፣

   (ለ) ባንክ የደረሱ ሰነዶች እርማት የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝና ይሄው ተስተካክሎ እስኪቀርብ ጊዜ የወሰደ መሆኑ በሚመለከተው ባንክ ተረጋግጦ ሲቀርብ፣

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☏ +251 116 62 98 00
📠 +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

(ሐ) አንድ የባንክ ፈቃድ ቁጥር ለተለያዩ ሁለት አስመጪዎች በስህተት በመሰጠቱ ማስተካከያ ለማድረግ ጊዜ የወሰደ መሆኑ ተረጋግጦ የቀረበ እንደሆነ፣

(መ) በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ተጓጉዘው አገር ውስጥ ለደረሱ ዕቃዎች በአዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ላለመውጣታቸው በአጓጓዡ ምክንያት መሆኑን ገልጾ ለዚሁ በጽሑፍ ማረጋገጫ ሲሰጥ፣

(ሠ) የዕቃው የመጋዘን ቆይታ ጊዜ የሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን የህዝብ በዓል ቀን ወይም የዕረፍት ቀን የሆነ እንደሆነ በቀጣዩ የሥራ ቀን ዲክላራሲዮን ለፌስቬት ማቅረብ እንደሚችል ሲረጋገጥ፣

(ረ) የጉምሩክ ሲስተም ባለመስራቱ ምክንያት ሰነድ ፌስቬት ማስገባት አለመቻሉ ሲረጋገጥ፣

(ሰ) ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ድርጅቶች፣ ኢምባሲዎች፣ ቆንስላ ጽ/ቤቶች እና የዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው ግለሰቦች ለሚያቀርቡት የዕቃ የመጋዘን ቆይታ ማራዘሚያ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣

(ሸ) በስጦታ የሚላክ የግልና የቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች እና ተመላሽ ኢትዮጵያውያን ለሚያቀርቡት የዕቃ የመጋዘን ቆይታ ማራዘሚያ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣

(ቀ) ዕቃው ከደረቅ ወደብ በማሻሻያ አዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ከመጋዘን ያልወጣው በቀረጥ ነጻ መብት ፈቃጅና ተቆጣጣሪ መ/ቤት ምክንያት ከሆነና ለዚሁ በጽሑፍ ማረጋገጫ ሲቀርብ፣

(በ) ሌሎች በአስመጪው የሚቀርቡ ከአቅም በላይ የሆኑ በቂ ምክንያት ሲቀርብ የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ሲራዘም ይችላል፣

2. የጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቅደው የኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊ

(ሀ) ከላይ በተራ ቁጥር 1 በተጠቀሱት ምክንያቶች ለሚቀርብ የዕቃ የመጋዘን ቆይታ ጊዜ የይራዘምልኝ ጥያቄ በቅ/ጽ/ቤቱ የኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ስራ አስኪያጅ በኩል መረጃው ተጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ይቀርባል፣

(ለ) የቅ/ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ የዕቃው የመጋዘን ቆይታ ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ ጊዜ ጀምሮ ከአስር ቀን ላልበለጠ የጊዜ ገደቡን ማራዘም ይችላል፡፡ ሆኖም በአስር ቀናት ውስጥ አሳማኝ በሆነ ምክንያት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለመፈፀም ያልቻለ እንደሆነ ለተጨማሪ አምስት ቀን ላልበለጠ ጊዜ ሊራዘም ይችላል፡፡

(ሐ) ከላይ በተራ ቁጥር 3 በፊደል ተራ (ሀ) መሰረት በተፈቀደ ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ሥነ - ሥርዓት ለመፈፀም ያልተቻለ እንደሆነ የማራዘሚያ ጥያቄው በጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ተጣርቶ በሚቀርብ የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በኮሚሽነሩ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3. የመጋዘን ጊዜ የቆይታ ጊዜ አቆጣጠር

የዕቃዎች የመጋዘን ቆይታ ጊዜ እንደ አንድ ቀን የሚቆጠረው በየብስ ተጓጉዘው ለሚመጣ ዕቃ ትራንዚት ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ፤ በአየር ተጓጉዞ ለሚመጣ ዕቃ ዕቃው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ 24 ሠዓት የሞላው እንደሆነ ነው፡፡

4. ሪፖርት ስለማድረግ

(ሀ) በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የተሰጠ የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ማራዘሚያ መረጃ ተደራጅቶ በተዘጋጀው የሪፖርት መላኪያ ቅፅ መሠረት በየወሩ ሪፖርት ለኮሚሽኑ ኦኘሬሽን ዘርፍ ያቀርባል፣

(ለ) በዋናው መ/ቤት ደረጃ የተሰጠ የጊዜ ማራዘሚያ ውሳኔ በጉምሩክ ኦኘሬሽን ዘርፍ በኩል መረጃው ተደራጅቶ በተዘጋጀው ቅፅ መሠረት ሪፖርት ለኮሚሽነሩ ይቀርባል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>፡-

- ለገቢዎች ሚኒስቴር ጽ/ቤት
  <u>ገቢዎች ሚኒስቴር</u>፣
- ለጉምሩክ ኦኘሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ
  <u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>፣

# በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 1160/12 አንቀጽ 13 ንዑስ (11) መሠረት የመጋዘን የቆይታ ጊዜ ገደብ ማራዘሚያ

## መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ

| ተ.ቁ | የአስመጪው/ድርጅቱ ስም | የዲክ/ዮን ቁጥር | የተጠየቀበት ምክንያት | 20 በመቶ ቀረጥና ታክስ በቅጣት ቢከፈል ኖሮ | የቀረበው ማስረጃ | | የተራዘ መው ጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ማስረጃ የሰጠው አካል | የደብዳቤው ቁጥርና ቀን | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |

ያዘጋጀው :- ስም:_________________. ፊርማ:-_________________.

ማስተወሻ

1. ቅ/ጽ/ቤቶች በየወሩ ቅጹን ሞልተው ለጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ በወሩ መላክ አለባቸው፣
2. በጉምሩክ ኦፐሬሽን ዘርፍ ጽ/ቤት በኩል ከቅ/ጽ/ቤት የሚላኩ ሪፖርቶች ተደራጅተው ይያዛሉ፣
3. የተደራጀው መረጃ ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር እንደአስፈላጊነቱ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

ደበሌ ቃበታ ሆርዶ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር